# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

## ሁለተኛ ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም
## የቤተሰብ ዕቅድ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ፓኬጅ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ

ማውጫ ..... i
ምዕራፍ አንድ ፡የቤተሰብዕቅድ ..... 1
1.1. መግቢያ ..... 1
1.2.1. አጠቃላይዓላማ ..... 1
1.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች ..... 1
1.3 የሚከናወኑ ተግባራትና አተገባበራቸው ..... 2
1.3.1 ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም ..... 2
1.3.2 ከ1 ለ5 ትስስር እና የሴቶች ልማት ቡድን ጋራ መስራት ..... 3
1.3.3 የወንዶችን ተሳትፎ ማጎልበት ..... 3
1.3.4 ለተፅእኖ ፈጣሪ አካላት የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ፓኬጅ ማስተዋወቅ እና ማነቃቃት ..... 3
1.3.5 ቅንጅታዊ አሰራርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማጠናከር ..... 3
➢ በቀበሌ የሚገኙትን ደጋፊ አካሎችን መለየት ..... 3
1.3.6 በአካባቢው በሚገኙ የጤና ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎችን ድጋፍ መሻትና አብሮ መስራት ..... 5
1.3.7 ጥራቱን የጠበቀ ቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት ..... 5
1.3.7.1 ምክር አገልግሎት መስጠት ..... 5
1.3.7.2 የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎችን ለተጠቃሚዎች መስጠት ..... 5
1.3.7.3 የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ማቀናጀት ..... 6
1.3.7.4 የሪፈራል አገልግሎት መስጠት ..... 6
1.3.8 በቤተሰብ እቅድ ላይ የኮሚኒኬሽን የጤና ትምህርት ስራዎችን መስራት ..... 7
ስለቤተሰብ እቅድ ትምህርት መካተት ያለባቸው ቁልፍ ጉዳዮች ..... 7
1.3.9 መልካም ተሞክሮን መቀመርና ማስፋት ..... 8
1.4 የሚጠበቁ ውጤቶች ..... 8
1.5 ክትትልና ግምገማ ..... 8
1.6 ለፓኬጁ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችና የሥራ መሣሪያዎች ..... 9
ምዕራፍ ሁለት፡ የታዳጊዎችና የወጣቶች የተዋልዶ ጤና ..... 12
2.1. መግቢያ ..... 12
2.2. ዓላማ ..... 12
2.2.1. አጠቃላይ ዓላማ ..... 12
2.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች ..... 12
2.3. የሚከናወኑ ተግባራትና አተገባበር ..... 13
2.3.1. መሠረታዊ መረጃን መሰብሰብ ..... 13
2.3.2. ስለታዳጊዎችና ወጣቶች የጤና ፓኬጅ ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅና ማነቃቃት ..... 13
2.3.3. በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ውጤቱን ለኅብረተሰቡ መግለጽና በጋራ የሥራ እቅድ ማውጣት ..... 13
2.3.4. የ1ለ5 እና የልማት ቡድን መሪዎችና የአቻ ለአቻ አስተባባሪዎች / አስተማሪዎች ሥልጠና ማካሄድ ..... 14
2.3.5. ለፓኬጅ ስራ ደጋፊ ሊሆኑ ከሚችሉ ድጋፍ ሰጪ አጋሮች ጋር ቅንጅት መፍጠር ..... 14
2.3.6. መልካም ተሞክሮን ማስፋፋት ..... 15
2.3.7. የወጣቶች ቀን ማዘጋጀት ..... 15

2.3.8. አካባቢያዊና መንግስታዊ ህጎችንና ደንቦችን መጠቀም ............................................ 16
2.3.9. በትምህርት ቤቶች የወጣቶችና ታዳጊዎች ተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞችን ማስፋፋት 16
2.4. ጤና ጣቢያና የጤና ኬላ የሥራ ግንኙነት ........................................................................ 16
2.5. የሚጠበቁ ውጤቶች ........................................................................................ 16
2.6. ክትትልና ግምገማ .......................................................................................... 17
2.7 ለፓኬጁ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ መድኃኒትና ቁሳቁሶች ............................................. 18

# ምዕራፍ 1

# የቤተሰብ ዕቅድ

# ምዕራፍ አንድ ፡የቤተሰብዕቅድ

## 1.1. መግቢያ

የቤተሰብ እቅድ ማለት ግለሰብ ወይንም ጥንዶችበጋራ ወይንም በተናጠል ስንት ልጆች፣መቼ መውለድ እንደሚፈልጉና በልጆቻቸው መካከል ስለሚኖረው የእድሜ ልዩነት የሚወስኑበት ዘመናዊ የአኗኗር ዘዴ ነው። የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የእናቶችና ህጻናትን ጤንነት ለማሻሻልና ከህመምና ሞት ለመታደግ፣ ያልታቀደ እርግዝናን በዚህም ሳቢያ የሚከሰተውን ውርጃ ለመከላከልና እንዲሁም የተሻለ ኑሮ ለመምራት ያስችላል። በተጨማሪም ሴቶች በምርት እና በልማት ስራ ላይ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይረዳል።

በኢትየጵያ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ከ1940ዎቹ አካባቢ ጀምሮ በትልልቅ ከተሞች የተጀመረ ሲሆን አገልግሎቱ ቀስ በቀስ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች እየተሰፋፋ በገጠር ኗሪ የሆነውን ሕብረተሰብ ክፍልም ተጠቃሚ እየሆን መጥቷል ። በተለይም የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ የህብረተሰቡ ግንዛቤ እና የአገልግሎቱ ተደራሽነት እያደገ በመምጣቱ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ይገኛል። ይሁን እንጂ ሽፋኑ እየጨመረ ቢመጣም በክልሎች መካከል ያለው የአፈጻጸም ልዩነት ከፍተኛ ነው። ከነዚህም በተጨማሪ የአገልግሎት ጥራት መጓደል፣ ከፍተኛ የባህልና የእምነት ተጽእኖዎች መኖር፤ ወጣቶችን በአግባቡ ተደራሽ አለመሆናቸው፣ የአቅርቦት መቆራረጥ ወዘተ ዋና ዋና ክፍተቶችና ማነቆዎች ናቸው።

በመሆኑም ቤተሰብ ተኮር የሆነ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት በገጠር ውስጥ በማስፋፋት ሕብረተሰቡ ጥራት ያለው፣ ፍትሃዊ እና ተደራሽ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችልና ያሉ ማነቆዎችንና ክፍተቶችን በሚፈታ መልኩ እንዲተገበር ይህ ሁለተኛው ትውልድ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ፓኬጅ ተዘጋጅቷል። በዚህ ፓኬጅ የተጨመሩ አገልግሎቶች በክንድ ውስጥ የሚቀበሩ የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችን አወጣጥ እንዲሁም አይ ዩ ሲ ዲ አሰጣጥ እና አወጣጥን ያጠቃልላል።

## 1.2. ዓላማ

### 1.2.1. አጠቃላይዓላማ

አራርቆ በመውለድ፣ ያለታቀደና ያልተፈለገ እርግዝናን በማስቀረት በእናቶችና ህፃናት ጤንነት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ሕመምና ሞት መቀነስ ነው።

### 1.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ሕብረተሰቡበቤተሰብዕቅድበቂግንዛቤ፣ዕውቀትናክህሎትእንዲኖረውማድረግ፣
- የቤተሰብዕቅድአገልግሎትለሁሉምህብረተሰብክፍሎችተደራሽበማድረግያልተፈለገእርግዝናንመቀነ፣
- የቤተሰብዕቅድአገልግሎትጥራትንማሻሻል
- በቤተሰብዕቅድአገልግሎትይበልጥየወንዶችንተሳትፎማሳደግ፣
- በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ላይ የባህልና የእምነት ተጽእኖ እንዲቀንስ ማድረግ ።

## 1.3 የሚከናወኑ ተግባራትና አተገባበራቸው

### 1.3.1 ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም

**በቀበሌውስጥየሚገኘውንጠቅላላመረጃመዝግቦመያዝ**

- ❖ የህዝብ ብዛት
- ❖ የቤተሰብ ቁጥር በዕድሜ፣ በፆታ፣ በሐይማኖት፣በሥራ የገቢ ምንጭ፣ የልደት፣ የስደትና የሞት

**ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑትን መረጃዎችን መያዝ**

- ❖ በመውለድ እድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች ብዛት
- ❖ የቤተሰብ  እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት
- ❖ አገልግሎቱን ከየት እንደሚያገኙና እንደሚጠቀሙ
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት የማይጠቀሙ ብዛትና ለምን እንደማይጠቀሙ
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ የማይጠቀሙ ነገር ግን ለመጠቀም የሚፈልጉ በተለይ ከ15-49 ዕድሜ ክልል ያሉ ብዛት
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት በመጠቀም ላይ የነበሩና ያቋረጡ ካሉ ያቋረጡበት ምክንያት
- ❖ የሚያጠቡ እናቶች ቁጥር

**መረጃዎች  ከየትና እንዴት ይሰበሰባሉ ?**

- ❖ መዘግብቶችንና ሪፖርቶችን በማገላበጥ
- ❖ በቀበሌ ደረጃ ከሚገኙ የተለያዩ  ሴክተሮች (ለምሳሌ፡- ቀበሌ አስተዳደር፣ ት/ቤት፣ ግብርና ወዘተ)
- ❖ ቤት ለቤት በመሄድና ከቤተሰቦች ጋር ውይይት በማድረግ፣
- ❖ ከነዋሪዎች አንዳንዶችን በመሰብሰብ እና ውይይት በማካሄድ፣

**መረጃውን መነሻ በማድረግ ወቅታዊ እቅድ ማዘጋጀት፣ መፈጸምና  ሪፖርት ማድረግ**

- ❖ በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዙሪያ ያሉ ችግሮችንና ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ተግባራት በመለየት  ማቀድ፣
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሽፋንንና ጥራትን ለማሻሻል ማቀድ፣
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎችን  ተደራሽ ለማድረግ ማቀድ፣
- ❖ የተዘጋጀውን ዓመታዊ ዕቅድ በየሩብ ዓመቱ እና በየወሩ በመከፋፈል መፈጸም፣
- ❖ የስራ አፈጻጸም ሪፖርቱን በወቅቱን እና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለጤና ጣቢያ ሪፖርት ማድረግ፣

### 1.3.2 ከ1 ለ5 ትስስር እና የሴቶች ልማት ቡድን ጋራ መስራት

- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎችን በቤተሰብ ዕቅድ ዙሪያ ማሰልጠን
- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎች በስራቸው የሚገኙትን በወሊድ ዕድሜ ክልል ያሉትን ሴቶች መዝግበው እንዲይዙና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በእቅዳቸው እንዲይዙ ማድረግ
- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎች በስራቸው የሚገኙትን በወሊድ ዕድሜ ክልል ያሉትን ሴቶች ስለቤተሰብ እቅድ እንዲያስተምሩ ማድረግ
- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎች በስራቸው የሚገኙትን በወሊድ ዕድሜ ክልል ያሉትን ሴቶች የቤተሰብ እቅድ ስለመጠቀማቸው እንዲመዘግቡና እንዲከታተሉ ማስቻል
- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎችን እንደአስፈላጊነቱ በየቤታቸው በመጎብኘት ስራቸውን ማየት፣ ችግሮቻቸውን መፍታትና ማበረታታት
- በቤተሰብ እቅድ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን ከልማት ቡድኖች ጋር በየጊዜው መገምገም፣ የልምድ ለውውጥ ማድረግና የጋራ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ

### 1.3.3 የወንዶችን ተሳትፎ ማጎልበት

- በቀበሌ ደረጃ ወንዶች በብዛት የሚሳተፉባቸው አደረጃጀቶች ( የግብርና ልማት ቡድን ) ስለ ቤተሰብ እቅድ አስፈላጊነት እና ወንዶች ሚና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት
- የቤተሰብ ዕቅድ ባለመጠቀም ምክንያት በእናቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሰውን ችግር ማስረዳት እና ስለጥቅሙ ማስተማር፣
- ለወንዶች አማረጭ የቤተሰብ ዕቅድ መኖሩን ማሳወቅና ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ማስረዳት፣
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን በተመለከተ ወንዶችን/ባሎችን ያሳተፈ በቤት እና በጤና ኬላ ደረጃ ምክክር ማድረግ
- በቀበሌ ደረጃ በሚካሄዱ የሴቶች ኮንፈርንስ ላይ ወንዶችን/ባሎችን ተሳታፊ ማድረግ

### 1.3.4 ለተፅእኖ ፈጣሪ አካላት የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ፓኬጅ ማስተዋወቅ እና ማነቃቃት

- በቀበሌው ለሚገኙ ተጽእኖ ፈጣሪ አካላት (የኃይማኖት አባቶች፣ የጎሳ መሪዎች፣ የእድር መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የቀበሌ መስተዳደር አካላት ወዘተ) በቤተሰብ እቅድ ምንነትና አስፈላጊነት ዙሪያ አድቮኬሲ ስራ መስራት
- በቀበሌው ለሚገኙ ተጽእኖ ፈጣሪ አካላት ለጉዳዩ ስኬታማነት በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ህብረተሰቡን የማንቃትና የማስተማር ስራ እንዲሰሩ መጎትጎትና ማስተባበር
- በቀበሌው ከሚገኙ ተጽእኖ ፈጣሪ አካላት ጋር የተከናወኑ ተግባራትና የመጡ ለውጦችን በየጊዜው መገምገምና ልምድ ልውውጥ ማድረግ

### 1.3.5 ቅንጅታዊ አሰራርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማጠናከር

- **በቀበሌ የሚገኙትን ደጋፊ አካሎችን መለየት**
  - **የቀበሌ መሥተዳደር፡-** አስተዳደራዊ ድጋፍ እንዲሰጥ፣

- **ግብርና፡-** የልማት ሠራተኞች ድጋፍ እንዲሰጡ፣
- **ትምህርት፡-** ለመምህራን እና ትምህርት በመስጠት ራሳቸው ተጠቃሚ በመሆን፣ የአካባቢውን እንዲያስምሩ ሞዴል በሆን ወዘተ…፣
- በሴቶች/የወንዶች የተደራጁ  ልማት ሠራዊትን በማንቀሳቀስ ስለቤተሰብ እቅድ እንዲያስተምሩ፣
- **ማህበራት**(የሴቶች፣የወጣቶች ወዘተ..) በማመቻቸት አባላቶቻቸውን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ፣
- **የሐይማኖት ድርጅቶ፡-** መድረክ በማመቻቸት ተከታዮቻቸውን በመቀስቀስ እንዲያሳትፉ፣
- ***መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡-*** በቴክኒክና በቁሳቁስ ወዘተ.. በመደገፍ

- ከአጋር አካላት ጋር ውይይት ማካሄድና የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ
- ዕቅድና ፍላጎትን ማጣጣምና በትብብር መሥራት
- የተከናወኑ ተግባራትን በጋር መገምገም ወደፊት አቅጣጫ ማስቀመጥ

### 1.3.16 ግብዓት ማሟላት

- ❖ ለጤና ኬላው የሚያስፈልገውን የቤተሰብ እቅድ ግብዓት በዓይነትና በመጠን አስቀድሞ መተንበይ፣ መጠየቅና መሟላት
- ❖ በጤና ኬላው የሚገኙ የቤተሰብ እቅድ ግብዓትን በአግባቡ መመዝገብና መያዝ

### 1.3.6 በአካባቢው በሚገኙ የጤና ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎችን ድጋፍ መሻትና አብሮ መስራት

- ❖ እገዛ የሚያስፈልገውን ክፍተት መለየት፣
- ❖ የጤና ባለሙያዎችን ቴክኒካዊ እገዛ መጠየቅ፣
- ❖ በጋራ ተባብሮ መሥራት፡፡

### 1.3.7 ጥራቱን የጠበቀ ቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት

#### 1.3.7.1 ምክር አገልግሎት መስጠት

- ❖ አገልግሎቱን ፈልገው ወይንም ለሌላ አገልግሎት ለሚመጡ ተገልጋዮችን በመመሪያው መሠረት (ለምሳሌ፡ በየደረጃው የሚሰጡ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዓይነቶችንና ጥቅማቸውን፣ የጎንሽ ጉዳቶችንና መፍትሄዎቻቸውን ጭምር) ጥራቱን በጠበቀ መልኩ የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- ❖ ምርጫቸውን መሠረት በማድረግ ተገቢውን የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴ መስጠት፣ መከታተል እና ችግር ሲከሰት ችግሮቻቸውን በአፋጣኝ መፍታት ፣

#### 1.3.7.2 የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎችን ለተጠቃሚዎች መስጠት

**ሀ. የአጭር ጊዜ የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎች (ኮንዶም፣ ፒልስ፣ መረፌ፣ ድንገተኛ እርግዝና መከላከያ )**-ለአጭር ጊዜ የሚያገለግሉ የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎች ምርጫቸው የሆኑ ተጠቃሚዎች እንደየምርጫቸውና እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው እንዲሁም ስለጎንዮሽ ጉዳታቸው በአግባቡ በማስረዳት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**ለ. በክንድ ሥር የሚቀበሩ የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎች (ኢምፕላንትስ)**
**ኢምፕላንትስ አሰጣጥ፡** እያንዳንዱን አሰራር (procedures) ለተገልጋዮች አስቀድሞ መንገር/ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ ዋና ዋና የሚከናወኑ ተግባራት፡-

- ❖ ለፕሮስጀሩ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ማዘጋጀት
- ❖ ትክክለኛ የኢንፌክሽን መከላከል አሰራርን መከተል
- ❖ ኢምፕላንቱ በሚሰጥበት ቦታ ላይ (በላይኛው የውስጥ ክንድ ) ማደንዘዣ መስጠት
- ❖ ኢምፕላንቱ በሚሰጥበት ቦታ (በላይኛው የውስጥ ክንድ) ቆዳ ላይ በትንሹ መብጣት
- ❖ ኢምፕላንቱን በተበጣው ቆዳ ስር ማስቀመጥ
- ❖ ኢምፕላንቱን በተበጣው ቆዳ ስር ከተቀመጠ በኂላ የተበጣውን ቆዳ በፕላስተርና በፋሻ ማሸግ፡፡ የታሸገው መቼ እንደሚፈታና መደረግ ስለሚጋባው ጥንቃቄ ለተገልጋይዋ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

**ኢምፕላንትስ ማውጣት** (Implants Removal)

- ለፕሮስጀሩ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ማዘጋጀት
- ትክክለኛ የኢንፌክሽን መከላከል አሰራርን መከተል
- ኢምፕላንቱ ያለበትን ቦታ በትክክል ማረጋገጥና በሚወጣበት ቦታ ላይ (በላይኛው የውስጥ ክንድ) ማደንዘዣ መስጠት
- ኢምፕላንቱ በሚወጣበት ቦታ (ኢምፕላንቱ በገባበት አጠገብ) ቆዳ ላይ በትንሹ መብጣት
- ኢምፕላንቱን ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው መሣሪያ ( forceps) ቆንጥጦ ማውጣት
- ኢምፕላንቱን ከወጣ በኋላ የተበጣውን ቆዳ በፕላስተርና በፋሻ ማሸግ፡፡ የታሸገው መቼ እንደሚፈታና መደረግ ስለሚጋባው ጥንቃቄ ለተገልጋይዋ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡
- ተግልጋይዋ አዲስ ኢምፕላንት እንዲሰጣት ከፈለገች የቀድሞው ከወጣበት በላይ ወይንም በታች ቦታ ላይ አለበለዚያም በሌላኛው ክንድ ላይ መስጠጥ ይቻላል፡፡

**ሐ. በማህፀን ውስጥ የሚቀመጥ (ሉፕ)**

**የሉፕ ማስገባት ሂደት (በአጭሩ ሲጠቃለል)-እያንዳንዱን የስራ ሂደት ለተገልጋይዋ የማስረዳት አስፈላጊነት መዘንጋት የለበትም፡፡**

- ተገልጋይዋ ከማህጸን ጋር የተያያዘ የጤና ሁኔታ ማረጋገጥ (screening)
- ለፕሮስጀሩ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች /Speculum,Tenaculum,uterine sound እና ሌሎች/ማዘጋጀት እና በጥንቃቄ መጠቀም
- ትክክለኛ የኢንፌክሽን መከላከል አሰራርን መከተል
- ተገልጋይዋ በደንብ እስክትረጋጋ ድረስ እንድታርፍ ማድረግ
- ተገልጋይዋ ምን ማድረግ እንዳለባት በመምከርና ስለክትትል ቀጠሮ በመስጠት ማሰናበት

### 1.3.7.3 የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ማቀናጀት

የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ከሌሎች በጤና ኬላው ከሚሰጡ አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅቶ ሊሰጥ ይችላል፡፡ለምሳሌ፡- ከክትባት አገልግሎት፣ከህጻናት ጤና ክብካቤ፣ከወሊድና ድህረ ወሊድ፣ከስርዓተ ምግብና የእድገት ክትትል ወዘተ አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅቶ በመስጠት አጋጣሚዎችን ሁሉ ለመጠቀም ያስችላል፡፡

### 1.3.7.4 የሪፈራል አገልግሎት መስጠት

ተገልጋዮች በጤና ኬላ የማይሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ከመረጡ ወደ ሚቀጥለው የጤና ድርጅት ማስተላለፍ/መላክ ያስፈልጋል፡፡

**ማስታወሻ፡-** *የቤተሰብ እቅድ አሰጣጥን በተመለከተ ሊዚህ ተግባር የተዘጋጀዉን ራሱን የቻለ መመሪያ በትክክል መከተል ያስፈልጋል፡፡*

### 1.3.8 በቤተሰብ እቅድ ላይ የኮሚኒኬሽን የጤና ትምህርት ስራዎችን መስራት

- **የተናጠል ኮሚኒኬሽን** - ከግልሰቦችና ጥንዶች ጋር መወያየት በቤት ለቤት ጉብኝት ወይንም በጤና ኬላ ደራጃ ሊሆን ይችላል
- **የቡድን ኮሚኒኬሽን/ውይይት-** የቤተሰብ ውይይት፣ የ1ለ5 አባላት ውይይት፣ የልማት ቡድን ውይይት፣ ተማሪዎች ውይይት፣
- **የማህብረሰተሰብ ውይይት** ማድረግ

*ስለቤተሰብ እቅድ ትምህርት መካተት ያለባቸው ቁልፍ ጉዳዮች*

1. ሰለቤተሰብ እቅድ ምንነት
2. የቤተሰብ እቅድ ጠቀሜታዎች  ለምሳሌ፡- በጤና ፣ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ ጎዳዮች
3. የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች  -በሁለት እንደሚከፈል

ሀ/ **የተፈጥሮ መከላከያ ዘዴዎች** ፣ ስለ እያንዳንዳቸው የሚያስገኘው ጥቅሞችና ውስንነቶች

- ጡት ማጥባት
- በቀን አቆጣጠር
- የማህጸን ፈሳሽ በማየት
- የሰውነት ሙቀት በመለካት
- ከግብረ ስጋ ግኑኝት መታቀብ
- የወንድ የዘር ፍሬ ወደ ውጭ ማፍሰስ

ለ/ **ዘመናዊ የመከላከያ ዘዴዎች-** ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች የሚሰጡት ጥቅምና ሊያስከትሉ የሚችሉ መጠነኛ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ማስተማርና ተጠቃሚው በአግባቡ ከተጠቀመበት ውጤታማነቱን  ማስረዳት።

**ለአጭር ጊዜ የሚያገለግሉ**

- በአፍ የሚዋጥ
- የሴትና የወንድ ኮንደም
- በመርፌ የሚሰጥ
- ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ

**ለረዥም ጊዜ የሚያገለግሉ**

- በክንድ ቆዳ ስር የሚቀመጥ ኢምፕላንት
- በማህጸን ውስጥ የሚቀመት (ሉፕ)

**ለዘለቄታ የሚያገለግሉ**

- የሴት ዕንቁላል ማስተላለፊያ ባንቧ መቋጠር፣
- የወንድ የዘር ፍሬ ማስተላለፊያ መቋጠር፣

### 1.3.9 መልካም ተሞክሮን መቀመርና ማስፋት

- **በቀበሌ ወይም በመንደር ደረጃ፡-** መልካም ተሞክሮ ያላቸው ጎጦች/መንደሮች ወይንም የልማት ቡድኖች ዝቅተኛ አፈጻጸም ላላቸው ጎጦች/መንደሮች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ እና ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማስተባበር እና ማመቻቸት
- **በቤተሰብ ደረጃ፡-** የቤተሰብ እቅድ በአግባቡ የሚጠቀሙ ቤተሰቦችን እንደ አርአያ መጠቀምና ሌሎች ከእነርሱ ልምድ እንዲቀስሙ ማድረግ
- **በግለሰብ ደረጃ፡-** በአገልግሎቱ የረኩ ተጠቃሚዎችን በሞዴልነት በመጠቀም ህብረተሰቡን ማስተማር፣

## 1.4 የሚጠበቁ ውጤቶች

- ቤተሰቦች ስለቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የተሟላ መረጃ ያገኛሉ፤ ዕውቀታቸው ይዳብራል፡፡
- ቤተሰቦች የቤተሰብ እቅድ ተጠቃሚ ይሆናሉ
- ከቤተሰብ ገቢ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ቤተሰብ ይመሠረታል
- ቤተሰቦች የግል ህይወታቸውን በማሻሻል ገቢያቸው ፣ ይዳብራል፣ የቤተሰብን መተፋፈግን ይቀንሳል
- ካልተፈለጉ እርግዝናና ወሊድ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የህክምና ወጪን ይቀንሳል
- የሴቶችን የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ያሳድጋል
- የኮንዶም ተጠቃሚዎች ቁጥር ስለሚጨምር የኤች አይ ቪ/ ኤድስና ሌሎች አባላዘር በሽታዎች ስርጭት ይቀንሳል
- ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ድጋፍ የሚሰጡ ተጨማሪ የህብረተሰብ ክፍሎች ይፈጠራሉ
- የቅንጅታዊ አሰራር ባህል ይዳብራል
- ሰዎች ከሰዎች ዕውቀትና ልምድ በመቅሰም በራሳቸው ተነሳሽነት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ
- ያልተፈለጉ /ያልታቀዱ እርግዝናዎችን፣ ውርጃን እና የእናቶችና ህጻናት ህመምና ሞትን ይቀንሳል

## 1.5 ክትትልና ግምገማ

**ድጋፍናክትትልማድረግአፈጻጸሙንከሚመለከታቸውጋርበመሆንመገምገም (ከ1ለ5፣ ከልማትቡድን፣ ከቀበሌአመራርጋርወዘተ)**

- የ1 ለ5 ትስስር መሪዎች ከስራቸው ያሉትን አባላት፣ የልማት ቡድን መሪ ከስሩ ያሉትን የ1 ለ5 ትስስሮችን ያቀዱትን ለመተግበራቸው ክትትልና ድጋፍ ማድረጋቸውን ማስተባበር እና የሙያ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡
- አፈጻጸማቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መገምገም፣ በሚስተዋሉ ክፍተቶች ላይ የጋራ የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥና ተግባራዊነታቸው መከታተል፡፡

***መገምገሚያ ነጥቦች***

- በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ላይ ትምህርት መሰጠቱን (ሴት፣ ወንድ)
- ነባርና አዲስ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ
- በጤና ኬላ ደረጃ የሚሰጡ የእርግዝና መከላከያ አማራጮች በበቂ መጠን መኖራቸው
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነው ያቋረጡና ያቋረጡበት ምክንያት
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በሚጠቀሙት የዕቅድ አገልግሎት ዓይነት ለያይቶ መመዝገቡ፣
- ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ደረጃ በላይ የሆኑትን የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት እንዲያገኙ ወደ ሌሎች የጤና ድርጅቶች የተላኩና ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ብዛት መመዝገባቸው፤

***የግምገማ ማስፈፀሚያ ስልቶች***

- ቤት ለቤት በመዘዋወር
- የልማት ቡድንና የጤና ኬላው ሪፖርቶችን በማሰባሰብና በመተንተን
- ተገልጋዮችን በማነጋገር

***የፕሮግራም (የፓኬጅ) መለኪያዎች* /indicators/**

- በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ላይ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት (ወንድ፣ ሴተ)
- አዲስ ተጠቃሚዎች ብዛት በዓይነት፣
- በተከታታይ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ብዛት በዓይነት፣
- ተጠቃሚ  ሆነው ያቋረጡ ብዘት፣

## 1.6 ለፓኬጁ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችና የሥራ መሣሪያዎች

| ***የተለያዩ አይነት የጽንሰትመከላከያ ዘዴዎች*** | ***ህክምናና ሌሎች  ቁሳቁሶች*** |
|---|---|
| ❖ ኮንደም ( የወንድና የሴት) | ❖ ሲርንጅና መርፌ |
| ❖ ፒልስ (ጥምርና ነጠላ) | ❖ የህክምና ሳህን/ትሬይ |
| ❖ ዲፖፕሮቬራ | ❖ የደም ግፊት መለኪያ |
| ❖ ኢምፕላንትስ (ጃዴል፣ ኢምፕላኖን፣ ሳይኖ ፕላንት ወዘተ) | ❖ የሙቀት መለኪያ |
| ❖ ሉፕ | ❖ የክብደት መለኪያ ሚዛን |
| ❖ የድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ | ❖ ግላቭ |
| ***የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች*** | ❖ አድሄሲቭ ፕላስተር |
| ❖ ማደንዘዣ (ሊዶኪን) | ❖ ባንዴጅ/ጎዝ/፣ጥጥ |
| | ❖ መመርመሪያ አልጋ |

| | |
|---|---|
| ❖ አድሬናሊን<br><br>❖ አዮዲን/ሳቭሎን<br><br>❖ የሉፕ እና ኢምፕላኖን ማስገቢያና ማዉጫ ኪቶች<br><br>❖ አስፈላጊ የሆኑ ጸረ- ተዋህስያን መድሃኒቶች (Amoxacillin, Ampicillin, metronidazole, Cotrimoxazole, Procaine pencillin ) | ❖ የማዋላጃ አልጋ<br><br>❖ ሴፍቲ ቦክስ<br><br>❖ ሎግ ቦክ (መከታተያ ቅጽ)<br><br>❖ የመስተማሪያ ቁሳቁሶች (የቤተሰብ ጤና መምሪያ፣ ቤተሰብ እቀድ ማስተማሪያ ቻርት (FP decision making tool), የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት መመሪያዎች ወዘተ.)<br><br>❖ የጽሕፈት መሣሪያዎች |

# ምዕራፍ 2

# የታዳጊዎችና የወጣቶች የተዋልዶ ጤና

# ምዕራፍ ሁለት፡ የታዳጊዎችና የወጣቶች የተዋልዶ ጤና

## 2.1. መግቢያ

ወጣቶች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሮአዊና ማህበራዊ ለውጦች የሚከሰቱበት የዕድሜ ክልል ላይ በመሆናቸው አጠቃላይ የህይወታቸው ሁኔታ ልዩ ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ወጣቶች ጥንቃቄ ለጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት፣ ላልተፈለገ እርግዝና፣ ያለ ዕድሜ ልጅ መውለድ፣ ለአደጋ የሚያጋልጥ ውርጃ፣ የራስን ህይወት ማጥፋት፣ ለተለያዩ ወሲባዊ ጥቃቶች፣ ኤች አይ ቪ ኤድስንና ሌሎች አባላዘር በሽታዎች፣ ለስራ አጥነት፣ ለድህነትና ለወንጀል ድርጊቶች የተጋለጡ ናቸው፡፡

በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ የታዳጊዎችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ፕሮግራም በማካተት ልዩ ትኩረት ተሰጥተዋቸው የተሻለ ህይወት በመምራት ጤናማና ብቁ ተተኪ ትውልድ እንዲሆኑ ማነኛውንም ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ታዳጊዎችና ወጣቶች ጤንነታቸው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ እርስበራሳቸው ተደራጅተው በበርካታ የተዋልዶ ጤና ችግሮቻቸው ዙሪያ እንዲወያዩና የባህርይ ለውጥ በማምጣት ራሳቸው ከአደጋ መከላከል እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የተዋልዶ ጤና አገልግሎት በገጠር ውስጥ በማቅረብ እና በማስፋፋት ሕብረተሰቡ ጥራት ያለው፣ ፍትሃዊ እና ተደራሽ አገልግሎት እንድያገኝ የሚያስችል እንዲሁም ማነቆዎችንና ክፍተቶችን በሚፈታ መልኩ ለመተግበር ይህ ሁለተኛ ትውልድ የታዳጊዎች እና ወጣቶች የተወልዶ ጤና አገልግሎት ፓኬጅ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ ፓኬጅ የተካተቱ አገልግሎቶች የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶች፣ የአባላዘር እና ኤች ኣይ ቪ ኤድስ በሽታዎች ምርመራ እና ሕክምና፣የውርጃ አገልግሎቶች፣አላስፈለጊ ሱሶችን፣መጠጦችን እና አደንዛዥ እፆችን የመታደግ ስራዎች፣ የክትባት እና አይረን አገልግሎቶች እንዲሁምበወላጆች እና ታዳጊዎች ግልፅ የስነ ተዋልዶ ውይይት ማድረግንያካትታል፡፡

## 2.2. ዓላማ

### 2.2.1. አጠቃላይ ዓላማ

ታዳጊዎችና ወጣቶች የተዋልዶ ጤናቸው በተሟላ መልኩ ተጠብቆ በአካል፣ በመንፈስና በማህበራዊ ኑሮ ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

### 2.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በታዳጊዎችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ችግሮችን የሚያስከትሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መቀነስ፣
- ታዳጊዎችና ወጣቶች ከኤች አይ ቪ ኤድስና ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ራሳቸውንና ማህበረሰባቸውን መጠበቅ እንዲችሉ ማድረግ፣
- ታዳገዎችና ወጣቶች ለማይፈለግ እርግዝና፣ ጥንቃቄ ለጎደለው ውርጃና ለሌሎች ተዋልዶ ጤና ችግሮች እንዳይጋለጡ ማድረግ፣

- ታዳጊዎችና ወጣቶች የቤተሰብ ዕቅድ እና ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ
- ታዳጊዎችና ወጣቶች ከአደንዛዥ ዕፆች፣ ሱስ የሚያስይዙ መድኃኒቶችና የአልኮል መጠጦች ራሳቸውንና ማህበረሰባቸውን እንዲጠብቁ ማድረግ
- ታዳጊዎችና ወጣቶች የዕለት ተእለት ኑሮቸውን በበጎና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲወጡ የሚስችላቸው የህይወት ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድረግ፡፡

## 2.3. የሚከናወኑ ተግባራትና አተገባበር

### 2.3.1. መሠረታዊ መረጃን መሰብሰብ

- መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ማደራጀት
- ከቀበሌ አመራር ጋር ውይይት ማካሄድና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ
- መረጃ መሰብሰብና ያለውን ወቅታዊ አድርጎ መጠቀም
- በታዳጊነትና በወጣትነት የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች ብዛት (በጾታ፣በዕድሜ፣በጋብቻ ሁኔታ፣ በሥራሁኔታ፣በትምህርት ደረጃ ወዘተ.የተከፋፈለ ሊሆን ይገባል፡፡)
- የቤተሰብ እቅድና ሌሎች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ እና ያልሆኑ ወጣቶች ብዛት
- የስነ-ተዋልዶ ክለብ ያላቸው ትምህርት ቤቶች ብዛት፣
- በቀበሌው በሚገኙ የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት የታቀፉ ታዳጊዎችና ወጣቶች ብዛት፣
- በተዋልዶ ጤና ዙሪያ የሠለጠኑ ወጣቶች/ታዳጊዎች ብዛት፣ (በጾታ)
- ወላጅ አልባ የሆኑ ታዳገዎች ብዛት፣ (በጾታ)
- ከወጣቶችና ታዳጊዎች ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች
- ታዳጊዎች ወይም ወጣቶች ያላቸው የተለያየ ክህሎት/ችሎታ፣

### 2.3.2. ስለታዳጊዎችና ወጣቶች የጤና ፓኬጅ ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅና ማነቃቃት

- የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማካሄድ
- ለመስተዳደር አካላት ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት የአድቮኬሲ ሥራ መሥራት
- ከህብረተሰቡ እና ከወጣቶች ጋር ውይይት በማድረግ መግባባት ላይ መድረስ
- ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሥልጠና መስጠት (ሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች ፣ መምህራን…..)

### 2.3.3. በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ውጤቱን ለኅብረተሰቡ መግለጽና በጋራ የሥራ እቅድ ማውጣት

- የተገኙ መረጃዎችን ማሰባሰብና ለዕቅድ ዝግጁ ማድረግ

- በጋራ የሥራ እቅድ ማዘጋጀት ውጤቱን ለታዳጊዎችና ወጣቶች  እንዲሁም ለኅብረተሰቡ መግለጥና በውጤቱ ዙሪያ መወያየት
- ቅድመ ጥናቱን መሠረት ያደረገና  ታዳጊዎችን፣ ወጣቶችን፣ኅብረተሰቡን ያሳተፈ  የሥራ እቅድ ማወጣት
- እንደአስፈላጊነቱ የሳምንት፣ የወር ፣ የሩብዓመት፣የግማሽ ዓመትና የዓመት የሥራ እቅድ ማውጣት

### 2.3.4. የ1ለ5 እና የልማት ቡድን መሪዎችና የአቻ ለአቻ አስተባባሪዎች / አስተማሪዎች ሥልጠና ማካሄድ

- ለሥልጠናው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችንና አጋዥ መሣሪያዎችን መለየትና ማዘጋጀት
- በመሥፈርቱ መሠረት ሰልጣኞችን መመልመል
- ከሰልጣኞች ጋር በሥልጠናው ዙሪያ ውይይት ማድረግ
- የሥልጠና ሥፍራና ጊዜ በጋራ መወሰን
- ሥልጠናውን ማካሄድ
- የመመረቂያ መሥፈርቱን ያሟሉትን ሠልጣኞች ማስመረቅ
- የአቻለአቻ አስተባበሪነት ስልጠና በመሥጠት ወደ ተግባር ማሰማራት፣
- ድህረ ስልጠና ክትትልና ግምገማ ማድረግ

### 2.3.5. ለፓኬጅ ስራ ደጋፊ ሊሆኑ ከሚችሉ ድጋፍ ሰጪ አጋሮች ጋር ቅንጅት መፍጠር

- በቀበሌው የሚገኙትን አጋዦችን (ደጋፊዎችን) መለየት
  - መስተዳደር ፡-  አስተዳደራዊ ድጋፍ እንዲሰጥ
  - ግብርና፡- ልማት ሰራተኞች ትምህርትና ድጋፍ እንዲሰጡ
  - ትምህርት፡- ለመምህራንና ተማሪዎች ትምህርት በመስጠት የአካባቢውን ህብረተሰብ እንዲያስተምሩ እና ሞዴል እንዲሆኑ፤ የወጣቶች ተወልዶ ጤና ክብባት እንዲያቋቁሙ  ወዘተ…
  - ማህበራት ( የሴቶች፣ የወጣቶች ወዘተ…)፡- አባላቶቻቸውን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ በታዳጊዎችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ላይ ድጋፍ እንዲያደር፣
  - የኃይማኖት ተቋማት  - ተከታዮቻቻን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ በታዳጊዎችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ላይ ድጋፍ እንዲያደርጉ፣
  - መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች - በቴክኒክና በቁሳቁስ ወዘተ. ድጋፍ እንዲያደርጉ
- ውይይት ማካሄድና የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ
- ዕቅድና ፍላጎትን ማጣጣም እና በትብብር መሥራት

**ለወጣቶችየሚሰጡዋናዋናየጤናአገልግሎቶችየሚከተሉትናቸው**

- በተዋልዶ ጤና ጉዳዮች ላይ መረጃና የምክክር አገልግሎት መሥጠት
- የአቻ ለአቻ ትምህርትን ጨምሮ በተለያዩ ዘዴዎች ጤናማ የወሲብ ባሕርያትን ማበልጸግ
- የድንገተኛ እርግዝና መከላከያን ጨምሮ ስለ ተለያዩ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች መረጃ፣ ምክርና ምቹ አገልግሎት ማቅረብ
- ስለኮንዶም ማስተማርና ማቅረብ
- የምክርና ምርመራ አገልግሎት (የእርግዝና፣የኤች.አይ.ቪ. ምክክርና ምርመራ) መስጠት
- የአባላዘር በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር
- የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ፣ የድኅረ ወሊድ እና የኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍን መከላከል አገልግሎቶች መስጠት
- የውርጃ አገግሎት ከጤና ጣቢያ መላክ
- ለታዳጊዎች የመንጋጋ ቆልፍ መከላከያ ክትባት እና አይረን መስጠት
- በወላጆች እና ታዳጊዎችግልፅየስነ ተዋልዶ ውይይት
- በየደረጃው ባሉ የጤና ተቋማት ተገቢውን የቅብብሎሽ ሰንሰለት መመሥረት

## 2.3.6. መልካም ተሞክሮን ማስፋፋት

- በቀበሌ ውስጥ ወጣቶች ያላቸውን ግላዊ ተሞክሮ እርስ በእርስ እንዲለዋወጡ የሚያስችል መድረክ በማዘጋጀት ተሞክሮን መጋራት፡፡
- መልካም ተሞክሮ ያላቸው ጎጦች/መንደሮችወይንም የልማት በቡድኖች ዝቅተኛ አፈጻጸም ላላቸው ጎጦች/መንደሮች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ እና ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማስተባበር እና ማመቻቸት
- በታዳጊዎችና ወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና ፓኬጅ ላይ የተሻለ ልምድ/ተሞክሮ ቤተሰቦችን እንደ አርአያ መጠቀምና ለሌሎች ከእነርሱ ልምድ እንዲቀስሙ ማድረግ

## 2.3.7. የወጣቶች ቀን ማዘጋጀት

- ፓኬጁን በስፋት ለማስተዋወቅ እንደአስፈላጊነቱ የወጣቶችን ቀን በቀበሌ ደረጃ በማዘጋጀት ህብረተሰቡን፣ አገር ሽማግሌዎች፣ ተማሪዎች፣ ታዳጊዎችና ወጣቶች፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች በመጋበዝ የታዳጊዎችና የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አግልግሎቶች ላይ ውይይት ማድረግ
- ወጣቶች የተለያዩ ሥራዎችንና የግል ተሞክሮአቸውን በበዓሉ ላይ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሌሎች ከእነርሱ እንዲማሩ ማድረግ

❖ በወጣቶቹና በታዳጊዎቹ የተዘጋጁ የተለያዩ ከተዋልዶ ጤና ጋር ቁርኝት ያላቸውን ተግባራት/ውጤቶች ለኅብረተሰቡ ማቅርብ፣

❖ ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ የተለያየ ድራማ፣ ጭውውት፣ፖስተርና ስዕላዊ መግለጫዎችን በማቅረብ

❖ በፓኬጁ ጥሩ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ላደረጉት ታደጊዎች፣ ወጣቶችና ቤተሰቦች እውቅና መስጠት፣ የማበረታቻ ሶጦታዎች እንዲሁም የምስክር ወረቀት መስጠት

### 2.3.8. አካባቢያዊና መንግስታዊ ህጎችንና ደንቦችን መጠቀም

❖ አካባቢያዊ ህጎችን ከመንግስት ህግና ደንብ ጋር አጣጥሞ መስራት

❖ ታዳጊዎች፣ ወጣቶችና የአካባቢው ነዋሪ በጋራ በሚወስኑት መሠረት የመተዳደሪያ ደንብ እንዲያወጡ ማድረግና መፈጸም

❖ ታዳጊዎችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤናን የሚመለከቱ በመንግስት የሚወጡ ህጎችን ተግባራዊ ማድረግ

### 2.3.9. በትምህርት ቤቶች የወጣቶችና ታዳጊዎች ተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞችን ማስፋፋት

❖ የተዋልዶ ክበባትን ማቋቋም

❖ የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አራማጆች መመልመል እና ማብቃት

❖ የሚኒ-ሚዲያ መስፋፋትን መደገፍና በተዋልዶ ጤና ዙሪያ እንዲሠሩ ማበረታታት

❖ የተለያዩ የሚሰራጩ ጽሑፎችን መበተን (በራሪ ጽሑፎች፣ ቡክሌቶች፣ ፖስተር፣ የተግባር ካርዶች ወዘተ.)

## 2.4. ጤና ጣቢያና የጤና ኬላ የሥራ ግንኙነት

በጤና ኬላ ደረጃ የሚከናወኑ የታዳጊና ወጣቶች ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ፡-

- ለተዋልዶ አገልገሎት የሚያስፈልጉ ግብአቶች ማሟላት
- የተዋልዶ አገልግሎት በትስስር መስጠት
- የሪፖርት ቅብብል እና ዕቅድ ዝግጅት
- የድጋፍ እና ክትትል

### 2.5. የሚጠበቁ ውጤቶች

❖ ወጣቶች ስለ ተዋልዶ ጤና በእድገት ምክንያት የሚከሰቱ ለውጦችና የመራቢያ አካላትን ተግባራት ያወቃሉ

❖ የወጣቶች የጤናና የማህበራዊ ችግሮች (ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈር፣ አደንዛዥ ዕጾች፣ አልኮል፣ ሀሽሽ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ የሴት ልጆች ግርዛት በመሳሰሉት) ችግሮች ላይ የተሟላ መረጃና ትምህርት በማግኘታቸውና የችግሮች ምንጭ በህብረተሰብ የጋራ ግንዛቤና ዕውቀት ይቀንሳሉ

❖ ወጣቶች ስለ ኤች ኤ ቪ ኤድስና ሌሎች በሽታዎች መረጃና ትምህርት በማግኘታቸው አንድ ለአንድ ጸንቶ መቆየትን ይመርጣሉ፣ ከጋብቻ በፊት ከወሲብ ይታቀባሉ፣ ልማዳዊ ድርጊቶችን ያስቀራሉ፣ ኮንዶም ይጠቀማሉ፡፡

❖ የወጣቶች የተዋልዶ ጤና ችግሮች የሆኑት ያልተፈለገ እርግዝናና ውርጃ እንዳይከሰቱ ወጣቶች የተለያዩ የእርግዝና መከላከያዎችን ተጠቃሚ ይሆናሉ

❖ ለወጣቶች ተስማሚና ምቹ የሆነ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ይስፋፋል፤ የቅብብሎሽ ሥርዓቱም ይጠናከራል ፣

❖ ከወሲብ መታቀብን ጨምሮ የኃላፊነት ስሜት ያለውና ጤናማ የተዋልዶ ጤና ባህሪ በወጣቶች ዘንድ ይሰርጻል፣

❖ ወጣቶች በተዋልዶ ጤና ዙሪያ ያሉባቸውን የጤና ችግሮች ለማስወገድ ወጣቶችን ሳቢ የሆኑ መድረኮች ይፈጠራሉ

❖ በቀበሌው ትምህርት ቤት የሚገኙ ሴት ተማሪዎች የወጣቶች ተዋልዶ ጤና ፕሮግራም ተጠቃሚ ይሆናሉ፣

❖ በትምህርት ቤቶች የወጣቶች ተዋልዶ ጤና ክበባት እና ሚኒ ሚዲያዎች ይቋቋማሉ፣

❖ የሕይወት ክህሎታችን ያዳበሩ ወጣቶች ቁጥር ይጨምራል፣

❖ ያለእድሜ ጋብቻ ይቀንሳል

❖ ያልተፈለገና ያልታቀደ እርግዝና ይቀንሳል

❖ በእርግዝና ምክንያት ትምህረታቸውን የሚያቋርጡ ወጣቶች ቁጥር ይቀንሳል

❖ የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አራማጆች ቁጥር ይጨምራል፡፡

## 2.6. ክትትልና ግምገማ

### ሀ. የክትትልና ግምገማ ነጥቦች

❖ የፕሮግራሙ አጠቃላይ ዓላማዎች እና የታቀዱት ዝርዝር ተግባራት መፈጸማቸውን

❖ የኅብረተሰቡ አካላት ስለታዳጊዎችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤና አስፈላጊነት ያላቸውን ግንዛቤአቸው መጨመሩን፣

❖ ትምህርት ቤቶች የተዋልዶ ክለቦች መቋቋማቸውንና በአግባቡ እየሠሩ መሆኑን፣

❖ ጎጂ ልማዳዊ ድርግቶች የተያዙ ወጣቶች ከድርጊታቸው ለመላቀቅ የሚያስቻለቸውን ተግባር እያከናወኑ መሆኑን፣

❖ ታዳጊዎችና ወጣቶች በቀበሌው በሚገኙ የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት ታቅፈው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን፣

- በተዋልዶ ጤና ዙሪያ የሠለጠኑ ወጣቶች/ታዳጊዎች የሚጠበቅባቸውን ተግባር እያስፋፉ መሆኑን፣
- ለወጣቶች የመወያያና የመማማሪያ መድረክ መፈጠሩንና ቀጣይነቱን መረጋገጡ፣
- ወላጅ አልባ የሆኑታዳጊዎች በኅብረተሰቡ የሚጠበቀውን እንክብካቤ እያገኙ መሆናቸውን፣
- ታዳጊዎች ወይም ወጣቶች ያላቸው የሕይወትና የተለያየ ክህሎት/ችሎታ እያዳበሩ መሆኑን፣
- ለተጨማሪ ሕክምና ወይም ለአገልግሎት ወደ ቀጠዩ የጤና እርከን የተላኩ ታዳጊዎችና ወጣቶች የሚጠበቀውን አገልግሎት ማግኘታቸውን፣

### ለ. የግምገማ ማስፈጸሚያ ስልቶች

- በመስክ ቤት ለቤት ጉብኝት በማድረግ እና ተገልጋዮች ማነጋገር፤
- በልማት ቡድንና የጤና ኬላ ሪፖርቶችን በማሰባሰብና በመተንተን የእቅዱን ስኬት ማረጋገጥ
- ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመሆን የግምገማ መድረኮችን በመፍጠር የተከናወኑ ተግባራት አፈጻጸምን ደረጃ መፈተሽ
- የክትትልና ግምገማ መለኪያዎችን በመጠቀም የአፈጻጸም ሁኔታዎችን መገምገም

### ሐ. የፕሮግራም (የፓኬጅ) መለኪያዎች /indicators/

- የተለያዩ የስነ ተዋልዶ ጤና መረጃዎችን ያገኙ ወጣቶች ብዛት/ ወንድ፡ሴት/
- የእርግዝና መከላከያ የሚጠቀሙ ወጣቶችና ታዳጊዎች ብዛት፣ /ወንድ፣ሴት/
- የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ታዳጊዎች/ወጣቶች ብዛት፣ (ወንድ፣ሴት)
- የአቻ ለአቻ አስተባባሪነት ሥልጠና የወሰዱ ታዳጊዎችና ወጣቶች ብዛት (ወንድ፣ሴት)
- የተደረጉ የአቻ ለአቻ ውይይቶች ብዛት፣
- የተቋቋሙ የተዋልዶ ጤና ክበባት ብዛት፣
- ኤች.አይ.ቪ. ምክክርና ምርመራ ያገኙ ታዳጊዎችና ወጣቶች ብዛት (ወንድ፣ሴት)

## 2.7 ለፓኬጁ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ መድኃኒትና ቁሳቁሶች

- የተለያዩ ተዋልዶ ጤና መረጃ የያዙ በራሪ ፅሁፎች፣ ፖስተሮች
- የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ከነኪቶቻቸው
- የኤች ኤይ ቪ ኤድስ እና አባላዘር በሽታዎች ምርመራና ህክምና የሚያገለግሉ መድሃኒቶችና ኬሚካሎች
- ማሰልጠኛና ማስተማሪያ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች/ቁሳቁሶች
- በአካባቢው እንደቤተመጻሕፍት የሚጠቅሙ ለንባብ የሚሆኑ ጽሁፎች
- መዝገቦች እና መመሪያዎች
- ቅጾች እና የጽሕፈት መሳሪያዎች